በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት

በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

**THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

**MINISTRY OF CULTURE & TOURISM**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት ኤጀንሲ

**ETHIOPIAN NATIONAL ARCHIVES AND LIBRARY AGENCY**

# የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቢብሎግራፊ 1998 ዓ.ም.

# NATIONAL BIBLIOGRAPHY OF ETHIOPIA 2005-2006

ቅፅ 24 ቁ. 2. 1998 ዓ. ም.

**Volume 24, No. 2, 2005-2006**

በሕትመት ማግኛና ዩኒየን ካታሎግ መምሪያ

በናሽናል ቢብሎግራፊ ቡድን ተዘጋጀ

ሰኔ 1998

**Prepared by**

**National Archives and Library of Ethiopia**

**Union Catalogue and Acqusition Department**

**(National Bibliography Team)**

**June, 2006**

# ብሔራዊ ቢብሎግራፊ

## (የደራሲያን አጭር የሕይወት ታሪክ)

# NATIONAL BIBLIOGRAPHY

## *(A SHORT BIOGRAPHY OF WRITERS)*

## **1998**

## **2005/06**

# የደራሲያን መዝገበ ህይወት ታሪክ



**ገብረሃና ገብረማሪያም (አለቃ)**
***( ካሜራ 1890 በሙሴ ሜርናስ )***
**(1797 - 1894 ዓ.ም.)**
***∩ ቁምነገራቸው ሁሉ በቀልድ የተሸፈነባቸው ሊቅ ∪***

ገብረሃና ገብረማሪያም በቤገምድር ጠ/ግዛት በደብረታቦር አውራጃ በፎገራ ወረዳ ልዩ ስሟ ናበጋ ጊዮርጊስ በምትባል ቦታ በ1797 ዓ.ም. ተወለዱ፡፡

ገብረሃና እቴጌ መነንን መዝሙርን፣ ውዳሴ ማሪያምንና ሌሎችንም አስተምረው ከጨረሱ በኃላ ለከፍተኛ የቤተክርስቲያን ትምህርት በእቴጌይቱ ት{ዛዝ ወደ ↓ንደር ተላኩ፡፡ ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኃላም በእቴጌይቱ ት{ዛዝ የአለቃነት ማ{ረግ ተሰጣቸው፡፡ ከዚያም ገብረሃና በ↓ንደር አካባቢ የሚገኙትን ቤተክርስቲያናት ብቃት በተሞላበት ሁኔታ ያስተዳደሩ ጀመር፡፡ እንደ ትልቅ ምሁር (አዋቂ) ይታዩ ጀመር ፡፡ በተለይ ፍትሐ ነገስትን በመተር↓ም የሚወዳደራቸው ወይም የሚስተካከላቸው አልነበረም፡፡

አፄ ቴዎድሮስ ስልጣን ከያዙና እራሳቸውንም ዳግማዊ ቴዎድሮስ ሁለተኛ ብለው ዙፋናቸውን በጫኑበት ጊዜ በሀገሪቱ ከፍትሐ ነገስት ሌላ የተፃፈ ሕግ ባለመኖሩ አለቃ ገብረሃና በተለይ ፍትሐ ነገስትን መሠረት በማድረግ ካሳ (ንጉሡ) ሀገርን እንዲያስተዳድሩ ይረዱዋቸው ነበር፡፡

አለቃ ገብረሃና በቅኔያቸው የሃይማኖት አለቆቻቸውን ( የበላዮቻቸውን ) ብቻ ሳይሆን የገነት ጌታን ∩ኵንኖ ኃጥአን ኩሎሙ አይደልወከ ምንተ፣ አፍቅሩ ፀላእተከሙ እንዘ ትብል አንተ ∪ ኃጥአንን በገሃነመ እሳት ማሰቃየትና መኰንን አይገባህም፣ ጠላትህንም እንደራስህ አድርገህ ውደደው የሚል ት{ዛዝ እንደሰጠህ ሁሉ ሀጢአተኞችንም ማወገዝና ወደ ሲ®ል መላክና ማሰቃየት የለብህም በማለት ∩ ፈጣሪያቸውን ∪ በመፈታተን ብዙ የምርምር ውጤቶችን አበርክተዋል፡፡ በዚህ ጥማቸውም የምርምር ቅኔ የሚል ልዩ የመጠየቂያ ወይም የመመርመሪያ መሳሪያ ይጠቀሙ ነበር ፡፡

በተጨማሪም ግብርና ለኢትዮ}ያ ኦርቶደክስ ቤተክርስቲያን ብሉይ ኪዳንንና አዲስ ኪዳንን በመተር↓ም ትልቅ አገልግሎት ቢያደርጉም ትልቁን አስተዋ+® ያደረጉት በሕግና በቤተክርስቲያን ዜማና አቋቋም ነበር፡፡ እንደዚሁም የፈጠሩት አዲስ ዓይነት የቤተክርስቲያን አቋቋም ከደብረታቦር ወደ ሸዋ እና ትግራይ

ተሰራጭቷል። ይህንንም አቋቋም ከብቸኛው ልጃቸው በኋላ ተክለ ብለው ሰየሙት። ይህም አቋቋም አስደሳችና ማራኪ ነው ተብሎ የሚገመት የአቋቋም ዘዴ ነው።

አለቃ ገብረሃና በአጠቃላይ ፈጥኖ መልስ በመስጠት ፣ ቃላትን በመሰነጣጠቅ፣ ሁለት ትርጉም በመስጠት፣ እናም ጠለቅ ያለ ትርጉም ያላቸውና ከተናገሩት በኋላ ቆይቶ ሊረዱት የሚቻል አገላለፆችን የሚጠቀሙ ነበሩ። አለቃ ገብርሃና በብዙ ከታወቁ የኢትዮ}ያ ነገስታት ዘመን በቅርበት የኖሩና በኢትዮ}ያ ሰማይ የምሁራን ሰማይ ላይም እንደ ንጋት ኮከብ ተደርገው ይታዩ ነበር።

በአለቃ ገብርሃና ተ૧] ከሚባለት መጻሕፍት ሌላ በአማርኛ ቋንቋ ስነጽሑፍ ውስጥ እሳቸውን ማጣቀስ ተገቢነት እንዳለው ምክንያት ተደር↓ ስለሚታይ በባህሪው ጠንካራና የተለየ ራስን በሰምና ወርቅ መሰል ልማዳዊ አገላለፆች በተከታታይ በእሳቸው ነፍስ የዘራ ፣ የታደሰ እና አዳዲስ የዚህ ዓይነቶቹ ምሳሊያዊ ጥበባዊ ፈጠራዎች እንደነበሩ በእሳቸው ስም የተዘጋ፱ እና አንድ ነገር በእሳቸው እንደተነገረ ተደርጎ ተወስዷል።

በመቅደላ ጦርነት አፄ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ በደ♥ዝማች ተክለጊዮርጊስና በደ♥ዝማች ካሳ ኋላ ላይ ዩሐንስ አራተኛ በተባለት መካከል ዙፋኑን ለመያዝ በተደረገው ጦርነት ደ♥ዝማች ካሳ ጦርነቱን ካሸነፉ በኋላ አለቃ ገብረሃናን ወደ ትግራይ በማስጠራት ፍትህን በፍትሐ ነገስት መሠረት እንዲያስተዳድሩ ጠየቋቸው። በዚህን ጊዜ አለቃ ገብረሃና ጥቂት መጻሕፍትን በብራና ላይ ጽፈው ነበር። እነዚህ የብራና ላይ ጽሑፎችም እስካሁን ድረስ በውስጣቸው የአለቃ ገብረሃና ስም ተፅፎ እንዳለበት በአክሱም ፅዩን ቤተክርስቲያን ወስጥ ይገኛሉ።

አለቃ ገብረሃና ትልቅ ዝና ያገኙት በዳግማዊ ሚኒልክ ፍ/ቤት ነበር። አለቃ ገብርሃና በጊዜያቸው በነበሩት ምሁራን በጣም ይታወቁ ነበር። ከእቴጌ ጣይቱና ከዳግማዊ ሚኒልክ ጋር ተባብረው በመስራታቸውም ዝናቸው ተሰራጨ። መጀመሪያ አለቃ ገብረሃና እንጦጦ በሚገኘው ቤተመንግስት ከዚያም በቅዱስ ኡራኤልና በቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን እንዲቆዩ ተደረገ። ነገር ግን ሀገራቸው ያለውንና በጣም የሚወዱትን ናበጋ ጊዮርጊስን በጣም ይናፍቁ ነበር። ሆኖም የሀገሪቱ ዋና ከተማ ወደ አዲስ አበባ በመዛወሩ አዲስ አበባ ለመቆየት አሰቡ። ውሎ አድሮ ግን ወደ ሀገራቸው ተመለሱ። ነገር ግን በአክሱም በ↓ንደር የቆዩትን ያህል በአዲስ አበባም እስከማይረሱ ለረ፱ም ጊዜ ቆይተው ነበር።

**ዘ ነ ብ (ደብተራ)**

በ18ኛው ም{ተ ዓመት የኖሩ ካህን፣ትውልዳቸው ሸዋ ተጉለት ነበር። ለትምህርት ጐንደር ተሻግረው በነበረበት ወቅት ከደጃች ካሣ /በኋላም አጼ ቴዎድሮስ/ ጋር ተዋውቀው ስለነበር ለእርሳቸው አደሩ። ቆይተሞ ከነገሡ በኋላ ጸሐፊ ትእዛዛቸው በመሆን አገልግለዋል። በዚህ ሥራ ላይ እንዳሉ ያዘጋጁት የዓጼ ቴዎድሮስ

የዘመን ታሪክ እስከ ዘመናችን ደርሶአል:: በይዘታውም ሆነ በአቀራረቡ ከፊተኞቹ የዘመን ታሪክ ከጻፉት ይለያል::

ዘነበ አጼ ቴዎድሮስን እስከ መጨረሻ ትንፋሻቸው ድረስ አልተለዩአቸውም:: መቅደላም በእንግሊዞች ሲያዝ እዚያው ነበሩ:: እንግሊዞቹም የደብተራ ዘነበን ማንነት በማወቃቸው ከዓለማየሁ ጋር በምርኮ ወሰዱአቸው:: በዚህን ወቅት ደብተራ ዘነበ ለዓለማየሁ ሞግዚት ሆነው ያገለግሉ ነበር:: ሆኖም ዓለማየሁ አልወደዳቸውም:: ስለዚህ ደብተራ መመለስ ግድ ሆኖባቸዋል::

ከውጭ አገር እንደተመለሱ አድዋ ለጥቂት ዓመታት ተቀምጠዋል:: ከዚያም ሆነው ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ይጻጻፉ ነበር:: በኋላም ወደ ሸዋ መጥተው ለንጉሥ ምኒልክ አማካሪ ሆነዋል:: በዚህን ጊዜ ሣይሆን አልቀረም ***መጽሐፈ ጨዋታ*** የሚለውን መጽሐፋቸውን የደረሱት:: ይህ መጽሐፍ በጊዜው ተወዳፅና በሰፊው የተነበበ ነበር:: ር{ሱ ግ{ዝ ጠቀስ ይሁን እንጂ የተጻፈው በአማርኛ ነበር:: በ1869 ዓ.ም. ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ወደ ጉራጌ አገር ዘምተው ነበረና እዚያ አረፉ:: ዘነበ በህይወታቸው ሣሉ ∩የቴዎድሮስ ታሪክ∪ እና ∩***መጽሐፈ ጨዋታ*** ∪ የተባሉትን ሁለት ሥራዎቻቸውን አሳትመዋል::

**ኪዳነወልድ ክፍሌ (አለቃ)**
**(1864-1937 ዓ.ም.)**

አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ በሸዋ ክፍለ ሀገር በይፋትና ጥሙጋ አወራጃ በ1864 ዓ.ም. ተወለዱ:: ለትምህርት ሲደርሱ በአካባቢያቸው የነበረውን የአገራቸውን ትምህርት ተማሩ:: በኋላም ወደ ጎንደር ተጉዘው የመጻሕፍትን ትርጓሜ አጠኑ:: በጊዜው የነበራቸው የቀለም አቀባበል፣ የሚስጥር መመራመርና መራቀቅ በጉባኤው ላይ ∩***የቀለም ቀንድ***∪ የሚል ቅጽል ተሰጣቸው::

አለቃ ኪዳነወልድ ከግዕዝና ከአማርኛ ሌላ አረብኛ፣ ኢብራይስጥኛ ፣ ላቲን፣ ሌሎችንም ቋንቋዎች አጠናቅቀው ያወቁ ነበር:: አለቃ ኪዳነወልድ በእየሩሳሌም ሃያ ሁለት አመት ተቀምጠዋል:: በዚህም ወቅት ብሉይና ሀዲስ በሦስት ቋንቋ ጠንቅቀው አመሣክረው ተርጉመዋል:: ኪዳነወልድ ክፍሌ በ1926 ዓ.ም. የመጀመሪያውን መዝገበ ፊደል አውጥተው ከልዩልዩ ቋንቋዎች ጋር በማመሳከር አሳትመዋል:: የአገራችን ፊደል አመጣጡንና ባህሉን በውል አስተባብረው በማቅረባቸውም በጊዜው ተቋቁመው ለነበሩት ትምህርት ቤቶች መመሪያና መማሪያ ለመሆን በቅተዋል:: ቀጥለውም ትንሽ አማርኛ ፊደል ከአረብና ከኢብራይስጥ አቆራኝተው አሳትመዋል::

አለቃ ኪዳነወልድ በተለያየ ዘይቤ ያቀርቧቸው የነበሩት ግጥሞች ለትውልድ ታላቅ ጥቅም ይሰጣሉ ተብለው የሚገመቱ ናቸው:: እንዲያውም አገራችን በምሥራቅ አፍሪቃ የብዙ ሺህ ዘመን ነፃ አገር ባለፊደልና ባለቋንቋ የሆነች እሷ ብቻ ስለሆነች ትውልድ ያገሩን ትምህርት በመጀመሪያ እንዲማር ያካሂዱት የነበረው

ቅስቀሳ በቀላሉ አይታይም፡፡ በአለም ስማቸው የገነነ የሥነ ጥበብ፣ የኪነጥበብ፣ የጽሑፍ ባለአጉዛዎች የሚደነቁባቸው በራሳቸው ቋንቋ ጽፈው ለአለም የአቀረቧቸው ሥራዎች ናቸው ይላሉ፡፡ አለም ሲመዝነው የግድ በተለያየ ቋንቋ ሊተረጉመው ይችላል ብለው ድጋፍ ይሰጣሉ፡፡

በሀገር ፍቅር እጅግ የተቃጠሉ፣ በፊደልና በቋንቋ እጅግ የኮሩና ለትወልድ ቋሚ ቅርስ ትተው ያለ| ሰው ነበሩ ፡፡ ለዚች አገር በአላቸው አቅም በብሔራዊ ስሜት ተነሳስተው ለታሪክ የሚቀርቡ በርከት ያሉ መጻሕፍት ጽፈው አሳትመዋል፡፡ በተለይም ከዘጠኝ መቶ ገጾች በላይ የሆነው ∩የሰዋሰው መጽሐፍ ∪ ታላቅ እንደሆነ ይነገራል፡፡ አለቃ ኪዳነ ወልድ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ታላቅ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሰው ነበሩ፡፡



**አፈወርቅ ገ/እየሱስ (ነጋድራስ) (1868 - 1947 ዓ.ም.)**

***∩ የዘመናዊ የአማርኛ የስነ ፅሑፍ አባት ∪***

አፈወርቅ ገ/እየሱስ በጐጃም ክፍለ ሀገር በባህር ዳር አካባቢ ዘጌ በምትባል ቦታ በ1868 ዓ.ም. ተወለዱ፡፡ በእንጦጦ ራጉኤል ቤተክርስቲያን ግድግዳ ላይ በሚቀቡት ቀለምና ስዕል ከእቴጌ ጣይቱ ጋር ባለመግባባታቸው እቴጌይቱ እስካልሞቱ ድረስ ወደ አገራቸው ላለመመለስ በመማል ከአልፍሬድ ኢልግ ጋር በ1894 ዓ፣ም፣ እ፣ኤ.አ. ወደ ስዊዘርላንድ ሄዱ፡፡ መጀመሪያ የአልፍሬድ ኢልግ ዘመድ በኋላም ጣሊያናዊቷን ዩጂኒያ ሮሲን በ1904 እ.ኤ.አ. አገቡ፡፡ ኔፐልስ ውስጥ ካለው ኦሪዬንታል ኢንስቲቱት ጋር ግንኙነት በማድረግ በኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍ ታሪክ የመጀመሪያው የአማርኛ ልብወለድ መጽሐፍ ለመሆኑ የሚነገርለትን ∩ ጦቢያ ∪ የተሰኘ ውን፣ የአማርኛ ሰዋሰው መሪ መፅሐፍ፣ ለኢትዮጵያ የራሳቸውን አስተያየት ያካተተ መጽሐፍ እንዲሁም የአጼ ምኒልክን የሕይወት ታሪክ ጽፈዋል፡፡ ከሥራ©ቻቸው ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ አጠቃቀማቸውና አገላለጻቸው " የዘመናዊ አማርኛ ሥነጽሑፍ አ∅ት " የሚል ሥም አሰጥቷχዋል፡፡

ነጋድራስ አፈወርቅ በሥነ ሥዕልና በሥነ ጽሑፍ ሥራ በጣም የተደነቁ ሰው ነበሩ፡፡ እነዚህን ሙያዎች በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር በመቅሰም የሚያስመሰግን የሥራ ፍሬ አሳይተዋል፡፡ ቀደም ብሎ እንደተገለፀው በሥዕል ሥራ ችሎታቸው የተለያዩ አብያተ ክርስትያናትን በሥዕል አስጌጠዋል፡፡

የማንተማቸው ልዩ ምልክት አድርገው የሚጠቀሙበትና በብዙዎቹ መጽሕፍታቸው ውስጥ የሚገኘ ውን ∩ ***ኢትዮጵያ ታብጽህ እፀዊሁ ሀበ እግዚአብሔር*** ∪ በሚል የሰየሙትን የሃሳብ ሥዕል የሳሉትም ራሳቸው ናቸው፡፡ነጋድራስ አፈወርቅ ትምህርታቸው ሥዕል ቢሆንም ቀደም ብለው ከሣሉአቸወ ሥዕሎች በስተቀር በሙያው ብዙም አልተጠቀሙበትም፡፡

እጅግ የሚደነቁበትና የሚመሰገኑበት ሙያ ሥነ ጽሑፍ ነው:: በኢትዮጵያ ይታተሙ ከነበሩት የቀድሞ ጋዜጦች ∩አእምሮ ፣ ብርሃንና ሰላም፣ የቄሣር መንግሥት መልዕክተኞች ∪ እና ሌሎች ጋዜጦች ውስጥ ቁጥራቸው በርከት ያሉ ጽሑፎችን አስፍረዋል:: የነጋድራስ ጽሑፍ ቋንቋው ጥራት ያለውና መልዕክቱ ልብ የሚገባ ቁም ነገር የያዘ ነው :: ድርሰቶቻቸውም ተነበው የማይጠገቡ ትዕይንቱ በዓይነ ልቦና ጕልተው እንዲታዩ የሚያደርጉ ስሜትን የሚማርኩ ናቸው:: ነጋድራስ አፈወርቅ ጠቃሚ የመማሪያ የታሪክና ልብወለድ መጻሕፍት አሳትመዋል::

ከዚህ በተጨማሪ ነጋድራስ አፈወርቅ ሦስት ያህል ቲያትሮች እንዳዘጋጁ፣ ነገር ግን ቲያትሮቹ አለመታተማቸውንና ለሕዝብ አለመታየታቸውን ፐርፌሰር ታምራት ወ/ሚካኤል ስለ ኢትዮጵያ ደራሲያን በጻፉት ጥናት ላይ ገልፀዋል:: የኢጣሊያንኛ እና የአማርኛ መዝገበ ቃላት አዘጋጅተውም ለመታተም እንደተሰናዳ በታሠሩበት ጊዜ ተወሰዶባቸዋል::

ነጋድራስ አፈወርቅ ገ/የሱስ በሥነጽሑፍ ሥራዎቻቸው አገራቸው እድትሰለጥን በተለያዩ ጽሑፎቻቸው ያመላከቱ ታላቅ ሰው ነበሩ::



**ኅሩይ ወልደሥላሴ (ብላቴን ጌታ)**

(1871-1931 **ዓ.ም.**)

***∩ የአማርኛ ቋንቋ የስነ ፅሁፍ ፋና ወጊ ∪***

ደን አቦ በሚባል ቀበሌ የተወለዱት ኅሩይ በወጣትነት ዕድሜአቸው ያሳዩት በነበረው ትጋትና ቅልጥፍና መምህር ወልደጊዮርጊስ ቀድሞ ይጠሩበት የነበረውን ሥም ገብረመስቀልን በመቀየር ኅሩይ አሉዋቸው፡፡ ትርጓሜውም ”ምርጥ” ማለት ነው::

ለአጼ ኃይለሥላሴ አማካሪ በመሆን የሚወጡትን የሃይማኖትና የአስተዳደር ሕጎች እየተረጐሙና የአርትኦት ሥራዎቻቸውን እያጠናቀቁላቸው እንዲወጡ ያደርጉ ነበር፡፡ በብላቴን ጌታ ኅሩይ ታሪክን ማኅበራዊ ጉዳይንና ፍልስፍናን ያካተቱ 42 የሚደርሱ መጻሕፍትን አዘጋጅተዋል፡፡ ከሥራ©ቻቸው ውስጥ፣ ” **ወዳጄ ልቤ** ” የሚባለው መጽሐፍ ታዋቂነትንና ተወዳጅነትን አትርፏላቸዋል::



**ገ/ሕይወት ባይከዳኝ**

(1879 -1912 ዓ.ም.)

ገ/ሕይወት ባይከዳኝ በ1879 ዓ.ም በአድዋ አካባቢ ተወለዱ፡፡ እድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ ኤርትራ ውስጥ በሚገኘው የስዊድን ሚሽን ሲማሩ ቆይተው ከዛም ወደ ጀርመንና አውስትራሊያ በመሄድ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ፡፡ ከጀርመን ሚሽን ጋር ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ በአጼ ምኒልክ ቤተመንግሥት ፀሐፊ በመሆን ሠርተዋል፡፡ የምኒልክ ሐኪም ለነበረው ጀርመናዊ ዶክተር አስተርጓሚ ሆነው ሲያገለግሉ ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በነበራቸው አለመግባባት አገር ለቀው ወደ ሱዳን ሄዱ፡፡ ከዛም ለሱዳን መንግሥት የሀገር ውስጥ ደህንነት ሲሰሩ ቆይተው ወደ ሀገራቸው በመመለስ በቤተመንግሥት ውስጥ ማገልገል ጀመሩ፡፡ በመቀጠልም የድሬዳዋ ጉምሩክ ኃላፊ ሆነው ተመድበው ባላባራስ ተፈሪና በሌሎች ተቀናቃ→ች ወገኖች ተፈጥሮ በነበረው ግጀት ራስ ተፈሪን ወግነህል በሚል ከሥልጣን ተወገዱ፡፡ በ1908 የመንግሥት ግልበጣ በኋላ ወደ ቀድሞው ሥልጣናቸው የተመለሱ መሆኑ ቢታወቅ በ1912 የህዳር በሽታ ተይዘው ለህልፈት በቁ፡፡

አከራካሪ የነበረው " ***መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር*** " በሃገሪቱ የውስጥ ጉዳይ አስተዳደርና ኢኮኖሚ እንዲሁም በትምህርት ላይ ፍጹም ለውጥ እንዲኖር የሚያሳስበው መጽሐፋቸው ለመጀመሪያ ጊዜ በአቶ ™ውሎስ ኖኞ አማካይነት በ1916ዓ.ም. ለህትመት በቅቷል፡፡

**ተሰማ ሀብተሚካኤል (1882 - 1962 ዓ.ም.)**

***∩ ለአማርኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላት ፋና ወጊ ∪***

ተሰማ ሀብተሚካኤል በሰሜን ሸዋ በሰላሌ አውራጃ ↓ሐጽዩን በ1882 ዓ.ም. ተወለዱ፡፡ ተሰማ የአባይን ወንዝ አቋርጠው ወደ ↓ጃም በመሄድ ዜማ፣ ግጥም፣ ትርጉም ቅኔን በተለያዩ ቤተክርስቲያናትና ገዳማት ትምህርታቸውን ይከታተሉ ነበር፡፡ በተለይ ዲማ በሚገኘው {ውቅ ገዳም በመሄድ ለቤተክርስቲያን ዜማና ግጥም

ትምህርት ሄደዋል፡፡ የቤተክርስቲያን ከፍተኛ ትምህርታቸውን ከተከታተሉ በኋላ በ1911ዓ.ም. በመንግስት ሥራ በመቀጠር ወደ ሐረርጌ ጠ/ግዛት ሄዱ፡፡ ተሰማ በቆን{ እፀ ጽሑፋቸውና በተለያዩ በፊደል አጣጣላቸው በኢትዮ}ያ ውስጥ እንደ ልዩ ጥበብ ተቆጥሮላቸው የታወቁ ነበር፡፡ ተሰማ ብዙ የሀይማኖት መፃሕፍትን እንዲገለብጠ ይታዘዙ ነበር፡፡

በጡረታ እስከተገለገሉበት 1954ዓ.ም. ድረስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት እንዲያዘጋፁ በትምህርትና ስነጥበብ ሚኒስቴር ኃላፊነት ተሰጣቸው፡፡ &ከሳቴ ብርሀን& የተሰኘው ሥራቸው ከጠንካራ ስራቸው ዋነኛ ሲሆን በእንግሊዝኛም የመጨረሻ ሥራቸው፣ እና ለአብዛኛው ሕዝብ ትልቁ ክንውናቸው ነበር፡፡ ከ1937 እስከ 1947 ዓ.ም. በዚህ መዝገበ ቃላት ዝግፅት ላይ ያዋሉዋቸው ፈጠራዎቻቸው እና ጥረት ብዙ ችግሮችንና መሰናክሎች ገጥመዋቸዋል፡፡ አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ቢሆንም በተጨማሪም ተሰማ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ አማርኛ ፣ አደሪኛ እና ግ{ዝ በደንብ በማወቃቸውና ይህንን የቋንቋ {ወቀታቸውን በዚህ መልካም ሥራ ላይ አውለዋል፡፡ ሁሉንም ጥንካሬያቸውን &ከሳቴ ብርሀን& የተባለው መዝገበ ቃላት ዝግፅት ላይ አውለውታል፡፡ ተሰማ ይህንን መዝገበ ቃላት ለማዘጋጀት ያነሳሳቸው ነገር ቢኖር በመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም ውስጥ ሲሰሩ በነበረበት ጊዜ በተማሪዎች አካባቢ የነበረው ለቃላት ትክክለኛውን ትርጉም የመስጠት ችግር መከሰቱን በመረዳት እና ብዙ የአማርኛ ቃላት በከተሞች አካባቢ በመረሳታቸውና በመጥፋታቸው እነዚህን የባህል ቅርሶች ለማቆየት ሲባል ነበር፡፡

ከአስር ዓመታት ጠንካራ ስራዎች በኋላ ባለ 1□398 ገፆች መዝገበ ቃላት ሲያዘጋጁ ፣ መዝገበ ቃላቱም 33□000 ድርሰቶችና አገባቦች 1,278 ስ{ሎች አሉት፡፡ የመዝገበ ቃላት ስራ ከ12 ዓመታት በኋላ በገበያ ላይ ዋለ፡፡ ስሙም ከሳቴ ብርሃን ተሰማ እንዲባልና ለደራሲው ክብር ሲባል እንዲሁም በትምህርትና ሥነጥበብ ሚ/ር ተመርጦ ተሰየመ፡፡ይህም ለተሰማ ሀብተሚካኤል እንደ ሽልማት ተቆጠረ፡፡

ይህ መጽሐፍ ለብዙ ዓመታት &ከሳቴ ብርሀን ተሰማ& ወይም &ከሳቴ ብርሀን& ከፋች ፣ ገላጭ ወይም ብርሃን አምጪ (ተሰማ) ብቸኛውና ጥሩ በገበያ ላይ ያለ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ነው፡፡



**እምሩ ኃይለ ስላሤ (ራስ) (1885 - 1972 ዓ.ም.)**

**∩ *ለውጥ ፈላጊና ደራሲ* ∪**

በሐረርጌ ጠ/ግዛት በጉርሱም ሕዳር 1885 ዓ.ም. ተወለዱ፡፡ ተወልደው በወራት ጊዜ ውስጥ እናታቸው ሞቱ፡፡ ዕድሜአቸው አራት ዓመት ሲሆናቸው እንደዚሁ ሌሎች ወላጆቻቸው ከሞቱባቸው ልጆች ከሚያድጉበት ከራስ መኮንን ቤት እየተማሩ እንዲያድጉ ተላኩ፡፡ እዚያም በአብዛኛው ግዕዝና ሌሎችንም ተማሩ፡፡

እምሩ ኃይለ ስላሴ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በጣም የሚታወቅ ስም ነው:: ከሚኒልክ ጊዜ ጀምሮ እስከ አብዮታዊት ኢትዮጵያ ረጂም ጊዜ መኖራቸው ደግሞ የበለጠ ለመታወቅና ጥሩ እድል እንዲኖራቸው አድርጓል::

ራስ እምሩ ኃይለ ስላሴ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በአብዛኛው በሀገር አመራር ላይ ሰፊ ቦታ የነበራቸው ቢሆኑም በአዛ□ነታቸው ፣በገ□ነታቸው ፣በዝነኛ ተዋጊነታቸው፣ በፖለቲከኛነታቸው፣ በጨዋነታቸውና ከጓደኞቻቸው ጋርም የነበራቸው ተግባብቶ የመስራት ችሎታቸውና ጥሩ ማሕበራዊ ግኑኝነታቸው እንኳንስ ከወዳጅና ከወገን በጠላቶቻቸውም ዘንድ ክብር አስገኝቶላቸዋል:: ከስነፅሑፍ ስራዎቻቸው ለኢትዮጵያ ፖለቲካ ዲፕሎማሲና ወታደራዊ ታሪክ ጎልተው ይታያሉ::

ራስ እምሩ ኃይለ ስላሴ እዚህ የስነፅሑፍ ስራዎች ውስጥ ሊካተቱ የበቁት ሦስት ልብ ወለዶች በመፃፋቸው ነው:: ከስነፅሑፍ ስራዎቻቸው ውስጥም ፡-

- የዓለም ትግል
- ፊታውራሪ በላይ
- ሰውና ዕውቀት የተሰኙት ሲሆኑ

የመጀመሪያው ስነፅሑፋዊ ስራቸው በአንዳንድ ምክንያቶች ሳይታተም ሁለተኛው ስራቸው መጀመሪያ ለሕትመት በቃ:: እንደዚሁ ሦስተኛው ስራቸው የመጀመሪያው ሳይታተም በሁለተኛ ደረጃ ሲታተም የመጀመሪያው ስራቸው በ1961ዓ.ም. ታተመ:: ይህ የመጀመሪያ ስራቸው በአብዛኛው ስለ ሀገር ዕድገት በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ውሰጥ ስለሚታየው ማሕበራዊ ሁኔታና ስለ ሌሎች የዓለም ሀገራት እድገት ወይም ስለ ስልጣኔ ወይም ስለ ዘመናዊነት የሚያወያይ ነው::

**ወልደጊዩርጊስ ወልደ ዮሐንስ ( ፀሐፊ ትዕዛዝ)**

**(1889 -1974 ዓ.ም.)**

በሸዋ ክፍለ ሀገር በምንጃር ወረዳ በ1889 ዓ.ም. ተወለዱ:: ብላታ ወልደጊዩርጊስ ወልደዮሐንስ በአካባቢያቸው ይሰጥ የነበረውን ትምህርት ከተማሩ በኋላ በሸዋ፣ በወሎና በጐንደር እየተዘዋወሩ ለአሥራ ስድስት ዓመታት ያህል የፅዋትወ ዜማ የቅኔና የመጻሕፍት ትርጉም ትምህርት ተከታትለው አጠናቀዋል፡፡

ብላታ ከሌሎች ሊቃውንት ጋር በመሆን ***መጻሕፍተ ሊቃውንትን*** ከግዕዝ ወደ አማርኛ ተርጉመዋል፡፡ በ1914 ዓ.ም. &ቤተ ሣይዳ& ይባል የነበረው ጋዜጣ ሲቋቋም ምክትል አዘጋጅ በመሆን፣ &***ብርሃንና ሰላም***& ***ጋዜጣና*** &***ከሣቴ ብርሃን ለልብ ጠቢባን***& ይባል የነበረው መጽሔት ዝግጅት አባል በመሆን አገልግለዋል፡፡ በኋላም የሰንደቅ ዓላማችንና የአዲስ ዘመን ጋዜጣን በኃላፊነት፣ ( በዲሬክተርነትና በረዳት ሚኒስትርነት) እንዲሁም የማስታወቂያ ሚኒስቴር አማካሪ በመሆን ለረጅም ዓመታት አገልግለዋል፡፡

እኚህ ታላቅ ጋዜጠኛና የሥነ ጽሑፍ ሰው አሥራ ሰባት ያህል መጻሕፍትንና እንዲሁም የተለያዩ መጣጥፎችን አዘጋጅተዋል፡፡ ከሥራዎቻቸውም ውስጥ በ1961 ዓ.ም ለህትመት የበቃው "**አግዐዚ**" የተሰኘው ልብወለድ መጽሐፋቸው ይጠቀሳል፡፡

ይህ መጽሐፍ የአንድ ወጣትን ወደ ውጭ ሀገር ለከፍተኛ ትምህርት መሄድና ተምሮም ወደሀገሩ በመመለስ ያየውን ሥልጣኔነና የተማረውን ትምህርት በሥራ ላይ ለማዋል የነበረውን ምኞትና ፍላጐት የሚተርክ ነው፡፡ መጽሐፉ ታሪካዊ ልብወለድ በመሆኑ የኢጣሊያን ከኢትዮጵያ መወጣትንና ድልን የሚያበስር ነው፡፡



**መኮንን እንዳልካቸው፣ (ራስ ቢትወደድ)** ፣

(1883 - 1963 ዓ.ም)

*( የመሳፍንት ፖለቲከኛና ወግአጥባቂ ፀሐፊ )*

መኮንን እንዳልካቸው በሰሜን ሸዋ በተጉለት አወራጃ አዲስጌ በምትባል ቦታ በ1883 ዓ.ም. ተወለዱ፡፡ በዳግማዊ ምኒልክ፣ በንግስት ዘውዲቱ እና በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሲያገለግሉ ነበሩ ፡፡ ቢትወደድ በሕይወት ዘመናቸው ከ20 በላይ መጻሕፍት በመድረስ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ዕድገት የጐላ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡ ከሥነ ጽሑፍ ሥራዎቻቸው ውስጥ የታተመው "**አርሙኝ**" የተባለው መጽሐፋቸው በጣም የታወቀ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ደራሲው የህይወት ታሪካቸውን ባጭሩ እንዲሁም በተለያዩ ጊዜያት የሠሯቸውን ስብስቦችን ስለማይጨው ጦርነትና የአለም ፖለቲካን በማካተት የፃፉት ነው፡፡



**መርስዔ ኀዘን ወልደቂርቆስ (ብላታ)**

**(1891 - )**

መርስዔ ሀዘን ወልደቂርቆስ በሸዋ ጠቅላይ ግዛት ፃሩ ቆላ ውስጥ እምባጮ መግደላዊት በሚባል ሥፍራ በ1891 ዓ.ም. ተወለዱ፡፡

ብላታ ትምህርት የጀመሩት በልፃነታቸው ሲሆን በጊዜው ዳዊት ደግመው ከዚያም  የዜማ ትምህርት በመጀመር ጾመድጓና ድጓ ዘልቀዋል፡፡ ቀጥሎም ቅኔ ተምረው ከአጠናቀቁ በ□ላ በ1905 ዓ.ም. የመጀመሪያ ሥራቸውን የወንበር ፀሐፊ በመሆን ጀምረዋል፡፡

የመጻሕፍት ሐዲሳትን ትርጓሜ፣ የዩሐንስ አፈወርቅን ትርጓሜ፣ እንዲሁም የመቅደመ ወንጌልን ትርጓሜ ትምህርትን ያጠናቀቁት እኚህ ታላቅ ሰው ብርሃንና ሰላም ጋዜጣ ሲመሠረት የጋዜጣው ዋና አዘጋፃ በመሆን ቀጥለውም የተፈሪ መኮንን ት/ቤት የግ{ዝና የአማርኛ አስተማሪ በመሆን ሠርተዋል፡፡ እንዲሁም ከ1933 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1963ዓ.ም. ድረስ በተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በኃላፊነትና በዲሬክተርነት ሲያገለግሉ ቆይተዋል፡፡

ሥነጽሑፍንና ታሪክን በተመለከተ አሥራ ሦስት መጻሕፍትን ጽፈዋል፡፡ ሰባት መጻሕፍትን ተርጉመዋል፡፡ የተለያዩ ጽሑፎችን አሰባስበው አዘጋፃተዋል፡፡ የቅዱሳት መጻሕፍት ሥራዎችን ከሊቃውንት ጋር በሆን አዘጋፃተዋል፡፡ ከሥራዎቻቸው ውስጥ በ1935 ዓ.ም. የተጻፈውና &**የአማርኛ ሰዋስው**&  የተሰኘው መጽሐፋቸው በወቅቱ የአማርኛ ሰዋስው መጽሐፍ ባለመዘጋጀቱና ተማሪዎችም ተገቢውን የቋንቋ ትምህርት ባለማግኘታቸው ይቸገሩ ስለነበር ይህንንም ችግር ለማቃለል ሲባል አዘጋጅተው አቅርበው ነበር፡፡



**ዮፍታሔ ንጉሤ** (1897-1937 ዓ.ም.)

ዮፍታሔ ንጉሤ በጐጃም ክፍለ ሀገር በደብረ ኤልያስ ቀበሌ በ1897 ዓ.ም. ተወለዱ:: እኚህ ታላቅ ሰው በርካታ ድርሰቶችን የጻፉ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች አብዛኞዎቹ ለሕትመት አልበቁም፡፡ ከጽሑፎቻቸውም 1928 ዓ.ም ውስጥ ለሕትመት የበቃው ∩***ጐበዝ አየን***∪ የሚለው መጽሐፋቸው ሲሆን በመጽሐፉ ተጠቃሎ የሚገኘው ፍሬ ሃሳብ የ1928 የጣሊያንን ወረራ አስመልክቶ ሕዝቡ በጀግንነት እንዲጋፈጠው የሚያበረታታና የሀገር ፍቅር ስሜትን የሚቀሰቅስ ነው ፡፡ ዮፍታሔ ንጉሤ በዘመናቸው ከነበሩት ዕውቅ የሥነ ጥበብ ሰዎች አንዱ ነበሩ፡፡



**ማኅተመ ሥላሴ ወልደመስቀል (ብላቴን)**
**(1897-1971 ዓ.ም.)**

የፈረንሣይ አገር የግብርና ተማሪ የነበሩት እኚህ ሰው ለልዑል አልጋወራሽ አስፋወሰን ፀሐፊ፣ የእርሻ ሚኒስትር ምክትልና ዋና ሚኒስትር፣ የገንዘብ ሚኒስትር፣ የሕዝብ አገልግሎት ሚኒስትር እንዲሁም የዘውድ አማካሪ በመሆን አገልግለዋል:: በታሪክ ፊት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠውና አጠቃላዩን የኢትዮ}ያን ሕዝብ ኢኮኖሚያዊ ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የሚዘከረውን ∩*ዝክረ ነገር* መጽሐፍ∪ በ1942 ዓ.ም. ለህትመት አብቅተዋል::



**ሀዲስ አለማየሁ (ዶ/ር) (1902- 1996 ዓ.ም.)**

*∩ የመንግስት ሹመኛና ዝነኛ ደራሲ ∪*

ደራሲ ሀዲስ አለማየሁ በ1902 በጎጃም ክፍለ ሀገር በደብረ ማርቆስ አውራጃ በጐዛመን ተወለዱ፡ የሀገራቸውን ትምህርት ከተከታተሉ በኋላ አዲስ አበባ መጥተው የዘመኑን ትምህርት ተምረው መምህር ሆኑ:: ጥቂት ጊዜ እንዳስተማሩ የፋሺሽት ኢጣሊያ ወረራ በመምጣቱ ወደ ጦር ግንባር ዘምተው ከተዋጉ በኋላ በአርበኝነት ትግሉን ቀጠሉ፡፡ ከዚያም ከራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ጋር በጣሊያን ሀገር ተግዘው ለዓመታት ቆዩ፡፡ ፋሺስት ኢጣሊያ ከሀገራችን በተባረረ በ3ኛው ዓመት አካባቢ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ፡፡

በድርሰት ዓለም የተሠማሩትም በወጣትነታቸው ወቅት ተማሪ ሳሉ ነበር፡፡ የመጀመሪያ የፈጠራ ድርሰታቸው "ያበሻና የወደኋላ ጋብቻ " የተሰኘ ተውኔት ሲሆን በወቅቱ ማለትም በቅድመ ፋሽስት ኢትዮጵያ የተመልካችን ቀልብ የሳበና ያስደሰተ ነበር፡፡ በተጨማሪም ከሕዝብ ጋር ያስተዋወቃቸው እና በ1958 ዓ.ም. ለህትመት የበቃውና በጊዜው የነበረውን ወግና ልማድ የሚገልጸው "ፍቅር እስከ መቃብር" የተባለው መጽሐፋቸው ነው፡፡

ሐዲስ ዓለማየሁ ልብ ወለድ ድርሰቶች እና ልብ ወለድ ያልሆኑ ጽሑፎችን አበርክተዋል፡፡ በኢትዮጵያ የስነ ጽሑፍ ዕድገት ወስጥ ሀዲስ ዓለማየሁ ከፍተኛ አስተዋፅዖ በማበርከታቸው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የዶክተርነት ማዕረግ ተሰጥቷቸዋል።



**ደራሲ ተክለጻድቅ መኩሪያ** (1906 - )

**∩ የታሪክ ባላባት ∪**

ደራሲ ተክለጻድቅ መኩሪያ በ1906 ዓ.ም. በሸዋ ተጉለትና ቡልጋ አውራጃ  ተወለዱ፡፡ ወደ አዲስ አበባ መጥተው የመጀመሪያ ትምህርታቸውን በአማርኛና በግዕዝ ካጠናቀቁ በኋላ በቀድሞው ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የፈረንሣይኛን ትምህርት ተምረዋል፡፡

ከልጅነት ጀምሮ መጻሕፍትን ማሰባሰብ የሚወዱት እኝህ ሰው ጣሊያን አዲስ አበባ ገብቶ ዝርፊያ በሚካሄድበት ጊዜ በጎህ ጽባህ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤቶች ከዶርዜ ሰፈር የተበታተኑ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን ይለቅሙ ነበር፡፡ ጣሊያን የሰበሰቡትን መጻሕፍት በመውሰድ እሳቸውን ይዞ ለሦስት ዓመታት አሠራቸው፡፡ ጣሊያኖች ተሸንፈው እንግሊዞች ከገቡ በኋላ ተመልሰው ቢስክሌት በመግዛት እየዞሩ ከጣሊያኖች ላይ ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ የሚያወሱ  መጻሕፍት መግዛትና መሰብሰብ ጀመሩ፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር እንደተቀጠሩ የኢጣሊያንኛ መጻሕፍት ወደ አማርኛ እንዲተረጉሙ ታዘው በመሥራት ላይ እንዳሉ ልጆች የሚማሩበት የታሪክ መጻሕፍት ጠፍቶ ፈረንጆቹ በራሳቸው ቋንቋ ታሪክ እንደሚያስተምሩ በመመልከታቸው ለምን በራሳችን ቋንቋ ታሪካችን አይፃፍም በማለት ቁጭት ያድርባቸዋል፡፡ በዚህም መደበኛ ሥራ እየሠሩ የታሪክ ጽሑፋቸውን መጻፍ ጀመሩ:: እኝህ
"የታሪክ ባላባት"  በመባል የሚታወቁት የታሪክ ሰው ጊዜያቸውን ሰለቸኝ ታከተኝ ሳይሉ በርካታ መጻሕፍትን በመድረስ ለህትመት አብቅተዋል፡፡

ደራሲ ተክለጻድቅ መኩሪያ የበለጠ የሚታወቁት በሥራ ዘመናቸው የእረፍት ጊዜያቸውን በመሰዋት ባዘጋጁዋቸው በኢትዮጵያ ታሪክ ጽሑፎቻቸው  ሲሆን ፣ በተጨማሪም የሥነ ጽሑፍ ሥራቸው " የሰው ጠባይና አብሮ የመኖር ዘዴ"  በ1943 ዓ.ም. የደረሱት መጽሐፍ ይገኝበታል፡፡



**ግርማቸው ተክለሐዋርያት (ደጃዝማች)**

**(1908 - 1980 ዓ.ም.)**

ደጃዝማች ግርማቸው ተክለሐዋርያት በሐረር ክፍለ ሀገር ሒርና ወረዳ በ1908 ዓ.ም. ተወለዱ፡፡ የአማርኛ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ ወደ ድሬዳዋ ተዛውረው አሊያንስ ሚስዮን የፈረንሣይ ትምህርት ቤት ተማሩ:: ከዚያም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በአልያንስ ሚሲዩን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ:: ለከፍተኛ ትምህርት ወደፈረንሣይ አገር ሄደው የዩንቨርስቲ ትምህርታቸውን በከፍተኛ ማዕረግ ጨርሰው ተመረቁ ፡፡ ከፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ በኃላ ደጃዝማች ግርማቸው በተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶች በኃላፊነት ከመሥራታቸውም ሌላ የኢትዮጵያ አምባሳደር በሆንም በተለያየ አገራት አገልግለዋል::

ደጃዝማች ግርማቸው ተክለሐዋርያት በሥነ ጽሑፍ ረገድ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ማድረጋቸው የሚታወስ ነው፡፡ ከሥነ ጽሑፋቻቸው ውስጥ "አርአያ" በሚል አርዕስት የጻፉት መጽሕፍ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነትን ከማትረ|ፉም ባሻገር በትምህርት ሚኒስቴር አማካይነት ለትምህርት መስጫ ተመድቦ ለወጣቶች የህሊና ብርሃን ለመሆን ችሏል:: የኢትዮጵያ ደራሲያን እንዲበረታቱ የድርሰት ሙያቸውም እንዲዳብርና እንዲስፋፉ የደራሲያን ማህበር በማቋቋምና የግል ገንዘባቸውን በመለገስ ለሙያው የነበራቸውን ታላቅ አክብሮትና ፍቅር አበርክተዋል ፡፡



**ደራሲ ከበደ ሚካኤል**
***(1909- 1991 ዓ.ም.)***

*በደብረብርሃን አካባቢ በገርሞ ገብርኤል ቀበሌ 1909 ዓ.ም ተወለዱ፡፡ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ የቤተክርስቲያን ትምህርት ተከታትለዋል፡፡ ከዛ በመቀጠልም በአሊያንስ ፍራንሴ ትምህርት ቤት ገብተው በጊዜው ከፍተኛ እስከነበረው ሰባተኛ ክፍል ድረስ ተምረዋል፡፡*

*አቶ ከበደ ሚካኤል 1930ዓ.ም. እስከ 1960ዓ.ም. ባሉት ዘመናት ከፃፏቸው ታላላቅ መጽሐፍት የምሁራንን አእምሮ ያጎለመሱ ፣ ግብረገብ ያስተማሩና ስለማህበራዊ ሕይወት የጻ| አባት መምህር እንደነበሩ ይታወሳል፡፡ አቶ ከበደ ሚካኤል ፍቅራቸው፣ ባህሪያቸው፣ ተፈጥሮአቸው፣ ስብእናቸው ድርሰት ነው፡፡ አቶ ከበደ ሚካኤል ከሀገራቸው ሳይወጡ ሁሉንም የትምህርት ዓይነት ቀስመዋል፡፡ በተጨማሪም ፈረንሣይኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ጣሊያንኛ ከማወቃቸውም በላይ ለደራሲነትም የበቁት በራሳቸው ፍላጐትና ስሜት ነው፡፡*

*አቶ ከበደ ሚካኤል የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ ያበረከቱት ላቅ ያለ አስተዋጽኦ ለመጀመሪያው የ1957ቱ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሽልማት ድርጅት የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ተሸላሚነት አብቅቷቸዋል፡፡ የአቶ ከበደ ሚካኤል ድርሰቶች የተዘጋጁት በስድ ንባብና በግጥም ሲሆን፣ በስድ ንባብ የተዘጋጁት ታሪካዊ ሲሆኑ ግጥሞቹ ደግሞ ፍልስፍናና ውስጠ ሚስጢር ያላቸው ናቸው ፡፡ የድርሰቶቻቸውም ቁጥር 91 ሲሆኑ 22 በአማርኛ የታተሙ ስልሣ ዘጠኙ ደግሞ ያልታተሙ ናቸው፡፡*

*አቶ ከበደ ሚካኤል በሥነ ጽሑፍ ሥራዎቻቸው በተለያየ የዕወቀት ዘርፍ ላይ የተካተቱ ሲሆኑ ለሀገሪቱ የሥነ ጽሑፍ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ታላቅ ደራሲ ነበሩ፡፡*



**ከበደ ደስታ ገብረ ማሪያም** (1910 - )

ከበደ ደስታ ገ/ማርያም በሸዋ ክፍለ ሀገር / ሜራ ሚካኤል / በ1910ዓ.ም ተወለዱ፡፡ እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ የቤተክህነት ትምህርት ቤት ገብተው ደረጃ በደረጃ ዜማ ፣ ቅኔ ፣ ትርጓሜና ሥነ ጽሑፍ ተምረዋል፡፡ ከበደ ደስታ የተለያዩ ቋንቋዎችን ያውቃሉ እነሱም ግዕዝ፣ ኦሮምኛ፣ እንግሊዝኛ ሲሆኑ ራሺያንኛን በመጠኑ ያውቃሉ፡፡

ከበደ ደስታ በተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶች ቦታዎች በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሠርተዋል፡፡ ይኸውም በትምህርት ሚኒስቴር በአስተዳደርና በትምህርት ሥራ በኃላፊነት ለሠላሣ ሁለት ዓመታት ፣ በሞስኮ ዩንቨርስቲ በአስተማሪነት ለሦስት ዓመት አገልግለዋል፡፡

ከበደ ደስታ በስነጽሑፍ በኩል ከፃፏቸው የተለያዩ ድርሰቶች በተጨማሪም ∩መስኮብኛ እና አማርኛ መዝገበ ቃላት∪ አዘጋጅተዋል። ለስነጽሑፍ ዕድገትም ከፍተኛ አስተዋፅዖ አበርክተዋል።



**መኮንን ዘውዴ ጐገና** (1914 - )

መኮንን ዘውዴ በወሎ ክፍለ ሀገር በ1914ዓ.ም. ተወለዱ፡፡ እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በወሎ ውስጥ በተንታ ግዕዝ ፣ የዜማ ትምህርት ተምረዋል፡፡ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት እየተማሩ በጉለሌ የእስካውት ትምህርት ቤት ሲከፈት በአዳሪነት እስከ 1927ዓ.ም. ድረስ ፈረንሣይኛ ቋንቋ ተማሩ፡፡ እንግሊዝኛና ጣሊያንኛም ቋንቋ በመጠኑ ያውቃሉ፡፡

መኮንን ዘውዴ በኢጣሊያ ወረራ ጊዜ ወታደር ለማሰልጠን ከቤልጂግ አገር ለመጡት አስተርጓሚ በመሆን ሠርተዋል፡፡ ከ14ዓመት ዕድሜ ሳይበልጡ በአምሳ አለቅነት ማዕረግ ማይጨው ዘምተው ቆስለው ተመልሰዋል፡፡ በአምስቱ ዓመት የመከራ ዘመን እስከ 1931 ዓ.ም. ድረስ በገጠር ሲኖሩ ወሎ ለጐ ሓይቅ ውስጥ በፋሽስቶች ታስረው ነበር፡፡ ከ1934 - 1969 ዓ.ም. ድረስ በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ በኃላፊነት አገልግለዋል።

መኮንን ዘውዴ ከሥራቸው በተጨማሪ በሥነ ጽሑፍ ላይ ትኩረት ይሰጡ ስለነበር የተለያዩ መጻሕፍቶችን ጽፈዋል። ከስነጽሑፍ ስራዎቻቸው ውስጥ ∩የማይጨው ቁስለኛ∪ የተሰኘው መጻሐፋቸው በህብረተሰቡ ዘንድ በጊዜው በጣም ይወደድ ስለነበረ በየትምህርት ቤቶች ውስጥ እንደማስተማሪያ መጻሕፍ ያገለግል ነበር።



**ነጋሽ ገ/ማሪያም** (1917 - )

∩ ***ተሰጥኦ ያለው የልብ ወለድ ደራሲና ጋዜጠኛ*** ∪

ነጋሽ ገ/ማሪያም 1917 ዓ.ም. በሐረርጌ ጠ/ግዛት በጨርጨር አወራጃ በሀብሮ ወረዳ ልዩ ስሟ መቻራ በምትባል አካባቢ ተወለዱ። ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በአካባቢያቸው ዳዊትን ፣ መዝመርን፣ ወንጌልንና የቤተክርስቲያን ዜማን ተማሩ።

ከጣሊያን ወረራ በኃላ የኢትዮጵያዊነት ስሜት ጎልቶ መታየት በመጀመሩ ጣሊያኖችን በብዙ ነገር ማውገዝና መቃውም ተጀመረ። እነሱም እንደ ሲጋራ ማጨስ፣ ሽርሙጥና የመሳሰሉት ነበሩ። ነጋሽ ይህን በተመለከተ ሽርሙጥና ምንም እንኳን በጣሊያኖች ጊዜ ይፋ በሆነ መንገድ ቢታይም ከዚያ በፊትም እንደነበረ ም ∩ሴትኛ አዳሪ∪ በተሰኘው መጽሐፋቸው ገልጸውታል።

ነጋሽ እንደ ፀሐፊ (ደራሲ) ችሎታቸውን ያሳዩት &ሴተኛ አዳሪ& የተሰኘውን ልብወለድ መጽሐፋቸውን በፃ|በት ጊዜ ነበር። በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይም የተለያዩ ጽሑፎችንና ግጥሞችን ይጽ⌋ ነበር። ነጋሽ በማስታወቂያ ሚ/ር በሬዲዮ ክፍል ውስጥ &የድል አጥቢያ አርበኞች& የተባለ ድራማ (ጨዋታ) ፅፈው ነበር። ነጋሽ ካበረከቷቸው ድራማዎች ውስጥ ∩የአዛውንቶች ክበብ∪ የተሰኘው አስቂኝ ድራማ ይገኝበታል።



**አሰፋ ገብረ ማሪያም**

አቶ አሰፋ ገብረ ማሪያም በሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት በጨርጨር አዉራጃ በሀብሮ ወረዳ መቻራ በምትባል አካባቢ ተወለዱ።

አሰፋ ገብረ ማሪያም ስለ ሽርሙጥና ማስፋፋት ችግር በጣሊያን ጊዜም ሆነ ከዚያ በኋላ & እንደ ወጣች ቀረች የሚል መጽሐፍ & በዚህም ስለሽርሙጥና አደገኝነት መወገዝ እንዳለበት ግብረገባዊ በሆነ መንገድ ይጽፉ ነበር። አሰፋ በ1949 ዓ.ም. ብቸኛዋንና የመጀመሪያዋን እንደወጣች ቀረች የተባለችውን ልብወለድ መጽሐፍ ፃፉ።



**ዓለማየሁ ሞገስ** (1918 -)

ዓለማየሁ ሞገስ በ1918 ዓ.ም. ተወለዱ። ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ባህላዊ ትምህርት ቤት ገብተው ዜማን ተማሩ። የአርበኝነት ግጥም እየገጠሙ የአርበ→ችን ወኔም ይቀሰቅሱ ነበር፡፡ በቤት ውስጥ የግዕዝን ዐዋጅ አገባብና የቅኔን ሥርዓት በአራት የወረራ ዘመናት ውስጥ ተማሩ፡፡ ከዚያም በ1936 ዓ.ም. በቅኔ መምህርነት ተመረቁ፡፡ በ1938 ዓ.ም. ዘመናዊ ትምህርት ጀመሩ፡ ከዚያም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በቋንቋና በታሪክ ሁለት የቢ.ኤ.ዲግሪና በኢጣሊያ አገር የሥነ ጽሑፍ ዲግሪ አግኝተዋል፡፡ በተጨማሪም ግዕዝ፣ ትግርኛ፣ ግሪክኛ፣ ኢጣሊያንኛ ፣ ፈረንሣይኛ፣ እንግሊዝኛ ቋንቋ ያውቃሉ ። ላቲን ፣ ዐረብኛና ቱርክ ያነባሉ፡፡

ዓለማየሁ ሞገስ በ1947 ዓ.ም. ጀምሮ በአስተማሪነት እንዲሁም ረዳት ፕሮፌሰር ሆነው በኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ክፍል ሠርተዋል:: የተለያዩ ለቋንቋ ማስተማሪያ የሚሆኑ ድርሰቶችን ጽፈዋል። ከሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎቻቸውም ውስጥም ∩ ገብረመስቀል ባሪያው ∪ የሚባለው ታሪካዊ ልብ ወለድ መጽሐፋቸው በሕብረተሰቡ ዘንድ ተደናቂነትን አትርፎላቸዋል።



***ግርማጽዮን መብራህቱ* (1918 - )**

***∩የመጀመሪያውን የትግርኛ መዝገበ ቃላት አዘጋጅ∪***

*መሪ ጌታ ግርማጽዮን መብራህቱ በኤርትራ ክፍለሀገር በ1918 ዓ.ም ተወለዱ ። ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በአካባቢያቸው የቤተክርስቲያን ትምህርት እየተማሩ አደጉ ። በየገዳማቱ እየተዘዋወሩ ጸዋትወዜማ ተማሩ ። እንደገና ወደጎንደር ተጉዘው ሙሉ ደብተራ የሚያሰኘው የዜማና የአቋቋም ሙያ አጠናቅቀው በመመረቅ ወደትውልድ ቀበሌያቸው ተመለሱ። በቀበሌያቸው በሚገኝ ቤተክርስቲያን በመሪ ጌትነት እያገለገሉ ብራና ፍቀው፣ መቃ ቆርጠው፣ ቀለም በጥብጠው፣ ብዙ የብራና መጽሐፍት ጽፈዋል።*

*መሪጌታ ግርማጽዮን በቤተክርስቲያን ትምህርት ሙሉ ዕውቀት ሲኖራቸው እስከ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ዘመናዊ ትምህርት ተምረው አጠናቀዋል። በወሎ ክፍለ ሀገር ይሰጥ በነበረው የመምህራን ኮርስ ተካፍለው በመምህርነት አገልግለዋል። የተለያዩ የማስተማሪያ የአማርኛ መጽሐፍትም አዘጋጅተዋል። ከዚያ ቀደም ሲልም ∩**የሀይማኖት ጋሻ ለጠላት መመለሻ**∪ በሚል ርዕስ ስለኢትዮጵያ አንድነት ፣ ስለሕዝቢ ጀግንነት የሚያወሳ መጽሐፍት ደርሰው አሳትመዋል። መሪጌታ ግርማጽዮን ታላቁንና የመጀመሪያውን የትግርኛ መዝገበ ቃላት ሲያዘጋጁ ያልዳሰሱት አውራጃ ያላገላበጡት መረጃ አይገኝም። በስድስት መቶ ሃምሣ ገጾች እና በሁለት መቶ ሃምሣ ስዕሎች የተቀነባበረው ∩**የትግርኛ መዝገበ ቃላት**∪ ቋንቋውን ለረሱ መቀስቀሻ ፣ ግዕዝ ለሚያውቁ መማሪያ የሚሆን ነው ።*

*መሪጌታ ግርማጽዮን በዚህ መዝገበ ቃላት ሥራቸው ለትግርኛ ቋንቋ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ቢባል ማጋነን አይሆንም። ይህም በሀገራችን የሥነ ጽሑፍ ዕድገት ውስጥ ከፍተኛውን ቦታ የሚይዝ ነው።*



**መንግስቱ ለማ**

(1920 - 1980 ዓ.ም.)

ደራሲ መንግሥቱ ለማ በ1920ዓ.ም. በአዲስ አበባ ተወለዱ፡፡ እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ከአባታቸው ቤት ሆነው ፊደል ቆጥረዋል:: በመቀጠልም በጸዋትወ ዜማ በኩል እስከ ድጓ በትርጓሜ መጽሕፍትም ሐዲሳትን ተምረዋል፡፡

በአገራችን ከሚገኙት እውቅ የብዕር ሰዎች አንዱ የሆኑት መንግሥቱ ለማ ዘመናዊ ትምህርትን ሐረር ከተማ በሚገኘው የስደተኞች ትምህርት ቤት ገብተው ተምረዋል:: ከዚያም ወደ አዲስ አበባ በመመለስ ኮተቤ መምህራን ኮሌጅ ትምህርት ቤት ገብተው ትምህርታቸውን አጠናቀዋል:: ከዚያም ወደ ለንደን በመሄድ ለስድስት ዓመታት የፖለቲካል ሳይንስና ኢኮኖሚስ ትምህርታቸውን ተምረው ጨርሰው ወደ አገራቸው ተመልሰዋል :: መንግስቱ ለማ የብዙ ድርሰቶች እንደዚህም በኮሜድና በትራጀዲ የተመሩ ቲያትሮች ደርሰዋል:: በህትመት የመጀመሪያ የሆነቸው ∩ የግጥም ጉባኤ ∪ ለሐሣብ፣ ለፍቅር፣ ለተረት ብለው ያቀነባበሯት በትምህርት ገበታ ላይም ሆነ በሥራ ያለው አንባቢ ሁሉ በቃሉ ያጠናት አስደሣች መፅሐፍ ነች:: በተለይም በመሬትና በጨረቃ መካከል የተደረገው የግጥም ወይይት ሥራቸው ግሩም ፍልስፍና ያለበት ሆኖ ይነበባል::

ደራሲ መንግስቱ ከግጥም ጉባኤ ሌላ የአባቶች ጫዋታ፣ ጠልፎ በኪሴ ፣ያላቻ ጋብቻና መጽሐፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ሀይሉ የተባሉት መጻሕፍት አዘጋጅተዋል:: የመንግስቱ ለማ የድርሰት ሥራዎች መካከል ያላቻ ጋብቻ በራሺያንኛና በእንግሊዝኛ ጠልፎ በኪሴም በእንግሊዝኛ ተተርጉመው ለአለም ህዝብ ገበያ ላይ ቀርበዋል:: የእንግሊዝኛው ተርጓሚ እራሳቸው ደራሲ መንግስቱ ለማ ሲሆኑ በእንግሊዝኛው ትርጉም ከአፍሪካ ደራሲያን ጋር ተወዳድረው አለም አቀፍ ሽልማት አግኝተውበታል::

ደራሲ መንግስቱ ለማ የብዙ ድርሰቶች እንዲሁም በኮሚዲና በትራጀዲ የተመሩ ትያትሮች ባለቤት ነበሩ ፡፡ ደራሲ መንግሥቱ ለማ ከሥነጽሑፎቻቸው ሌላ በተለያዩ የመንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ በከፍተኛ ኃላፊነት ላይ ሆነው አገልግለዋል::



**ብርሀኔ ጉቻለወርቅ ወልደሀና**

(1922 - )

ብርሀኔ ጉቻለወርቅ በሸዋ ክፍለ ሀገር ተጉለትና ቡልጋ አውራጃ በ1922ዓ.ም. ተወለዱ፡፡ እድሜያቸው ለትምህርት በደረሰ ጊዜም ትምህርታቸውን በመከታተል በማታ የንግድ ሥራ ትምህርት ቤት የምስክር ወረቀት አግኝተዋል፡፡ የእንግሊዝኛ ቋንቋም ችሎታ ነበራቸው ፡፡

ደራሲ ብርሃኔ ጉቻለወርቅ ጥቅምት 1923 ዓ.ም. በወታደርነት ፀሐፊ በመሆን በወር አምስት ብር ተቀጥረው ለአሥር ዓመታት ፣ በሲቪል ፀሐፊነት ደግሞ ለሀያ ዓመት አገልግለዋል።

ከ1953 ዓ.ም. ጀምሮ ድርሰት መጻፍ የጀመሩት ብርሃኔ ጉቻለወርቅ የጻፏቸው ድርሰቶች ከተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡

ከጻፏቸው መጻሕፍት ውስጥም፡ - ፈላስፋው ቃየል ነው ፣ እሬትና ማር ፣ የድሆች ጠበቃ ፣ ዳ→ች በፍርድ ላይ ፣ ባሌ መታኝ አለች ወይስ ፈታኝ የሚባሉት ይገኙበታል፡፡



**አቤ ጉበኛ (1925 - 1972 ዓ.ም)**

***∩ በመጻሕፍቱ ህይወትን የዘራ ብቸኛው ደራሲ ∪***

ባለቅኔ ደራሲና ገጣሚ የነበሩት አቤ ጉበኛ በ1925 ዓ.ም. በባህር ዳር ከተማ ተወለዱ፡፡
*በስድስት ዓመት ፊደል ቆጥረው ንባብ ተማሩ ቀጥሎም የቤተክርስቲያን ትምህርት ተከታተሉ፡፡ ከዚያም ወደ ደንጐላ ሔደው ቢትወደድ መንገሻ ጀምበሬ ተብሎ ይጠራ የነበረ ትምህርት ቤት እስከ ስድስተኛ ያደረጉት እርምጃ በጣም የሚያስደንቅ ነበር፡፡ ከዚያም ወደ አዲስ አበባ በመምጣት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀቁ፡፡*

*አቤ ጉበኛ በመጀመሪያ ሥራ የጀመሩት ማስታወቂያ ሚኒስቴር ቀጥሎ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሲሆን ፣ በመንግሥት ሥራ ከስድስት ዓመት የበለጠ አልቆዩም፡፡ ከዚያ ወዲህ ሕይወታቸውን የገ]ት በደራሲነት ነው፡፡ አቤ ጉበኛ ለትውልድ ቅርስ የሚሆኑ የተለያዩ ድርሰቶችን በአማርኛና በእንግሊዝኛ በመድረስ አሳትመዋል፡፡ ካሳተሟቸው መጻሕፍት በተጨማሪ " ቂመኛው ባሕታዊ " እና " የደካሞች ወጥመድ " የተባሉ ቲያትሮች አዘጋጅተው ለሕዝብ ታይቷል፡፡*

*በደራሲ አቤ ጉበኛ ብዕር ተከሽኖ የቀረበና በ1966 ዓ.ም. ዳግም ለህትመት የበቃው እና አብዮት በአገሪቱ ሲቀጣጠል በህብረተሰቡ ዘንድ በከፍተኛ ሁኔታ የተነበበው ∩ አልወለድም ∪ የተሰኘ ው መጽሐፍ ማንም ሰው ከእናቱ ማህጸን ጀምሮ ም©ትና ጥንቃቄ ሊለየው እንደማይገባ የሚያትት ሲሆን በመታየት ላይ ያለው እውነታ ግን አዳጋች የሆነና የሰው ዘር በድህነት ተወልዶ አድጐና ኑሮ በድህነት እንደሚያልፍ ያሳያል፡፡ እንዲህ ያለው ሁኔታ አግባብ አለመሆኑን የሚቃወመው ይሄው መጻሕፍ የሰው ልጅ የሚደርስበትን መከራ በመቃወም ይሞግታል የሰው ልጅ መብት በአግባቡ መጠበቅ እንዳለበትም ያስረዳል፡፡*



**ብርሀኑ ዘርይሁን (1925 - 1979 ዓ.ም)**

*∩ የልብወለድ ደራሲ ፣ የቲያትር ደራሲ ፣ ጋዜጠኛ እና ዜደኛ የፈጠራ ሰው ∪*

ደራሲ ብርሀኑ ዘርይሁን በ1925 ዓ.ም. በጎንደር ከተማ ተወለዱ፡፡ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ የቤተክርስቲያን ትምህርት ተምረዋል :: የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጎንደር ይገኝ በነበረው በቀድሞው የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ትምህርት ቤት አጠናቀቁ:: ከዚያም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በተግባረ ዕድ ትምህርት ቤት በሬዲዮ መካኒክነት ሙያ ተመረቁ፡፡

ሥራ የጀመሩትም በመምህርነት ነበር፡፡ በወቅቱ የካርታ ጂኦግራፊ ድርጅት በሜካኒክነት ሙያ ሠርተዋል፡፡ ከዚያም የጦር ሚኒስቴር እየተባለ ይጠራ በነበረው የአሁኑ ያገር መከላከያ ሚኒስቴር በአስተርጓሚነት ሠርተዋል፡፡ በ1921 ዓ.ም. ወደ ማስታወቂያ ሚኒስቴር እንዲዛወሩ ተደረገ፡፡ እዚያም የኢትዮጵያ ድምጽ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ነበሩ፡፡ ከሦስት አመት በኋላም የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆነው የማይረሳ ተግባር አከናውነዋል፡፡

ደራሲ ብርሃኑ ዘርይሁን የደረሱት ”አባነፍሶ ” &የለውጥ አርበኛ” እና ”ሞረሽ” የተባሉት ቴአትሮቻቸው የተወደዱ ድርሰቶች ናቸው፡፡ ከጻፉቸው መጻሕፍት ውስጥም የዕንባ ደብዳቤዎች እና የቴዎድሮስ ዕምባ እንዲሁም ለረጅም ተከታታይ ጊዜያት በኢትዮጵያ ሬዲዮ ሲተረክ የነበረው የአብዮት ዋዜማ፣የአብዮት መባቻና የአብዮት ማግስት የተሰኙት ይገኙበታል:: ደራሲ ብርሃኑ ዘርይሁን ለሀገራችን የስነ ጽሑፍ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ አበርክተዋል::



**አበራ ሞልቶት ታለ** ( 1925 - )

**ደራሲ አበራ ሞልቶት ታለ በመንዝ አውራጃ በ1925ዓ.ም. ተወለዱ ::  አበራ ሞልቶት እድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ አዲስ አበባ በአዳሪነት ትምህርታቸውን በመጀመሪያ የአንደኛና የሁለተኛ  ደረጃ  ትምህርታቸውን አጠናቀቁ፡፡**

አበራ ሞልቶት ሥራ የጀመሩት በትምህርት ሚኒስቴር በአስተማሪነት ሲሆን ፣ በመቀጠልም በዲሪክተርነት  በቢሮ ሠራተኝነት ከ1942 - 1952 ዓ.ም. ድረስ አገልግለዋል፡፡ ከ1953 - 1966 ዓ.ም. በሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር  በልዩ  ልዩ ደረጃ አገልግለዋል፡፡ ከ1966 ዓ.ም. ጀምሮ አገር አስተዳደር ሚኒስቴር ተዛውረው በምክትል የክፍል ሀገር አስተዳደሪነት ሠርተዋል፡፡

ደራሲ አበራ ሞልቶት የሥነ ጽሑፍ ዝንባሌ ስላላቸው የተለያዩ ድርሰቶችን በመድረስ መጻሕፍት አሳትመዋል፡፡



**™ውሎስ →→ (1926 -1984 ዓ.ም.)**

∩ *ጋዜጠኛና ደራሲ* ∪

ደራሲ ™ውሎስ →→ ህዳር 11 ቀን በ1926 ዓ.ም. ቁልቢ አካባቢ ተወለዱ፡፡ ™ውሎስ ባጋጠማቸው ችግር ምክንያት ትምህርታቸውን  ከ4ኛ ክፍል በላይ ለመቀጠል አልቻሉም ነበር፡፡ ብልህ አእምሮና የፈጠራ ችሎታ ስለነበራቸው በልጅነቱ   የኢትዮጵያ ጀግኖች አርበ→ች ጣሊያንን ሲገድሉ ወይንም ሲማርኩ ሥዕል  በመሳል ያሳዩ ነበር:: ™ውሎስ ካላቸው የጽሑፍ

ጥማት የተነሣ የ ∩ድምፅ ጋዜጣ∪ አዘጋጅ በመሆን የብዕር ድምፃቸውን ያሰሙ ነበር:: ጋዜጦች ላይ ከጽሑፍ አቅራቢነት እስከ አዘጋጅነት ለበርካታ አመታት ሠርተዋል:: በተለይ "አንድ ጥያቄ" አለኝ በሚለው በጋዜጣ አምዳቸው ላይ ታዋቂነትን አግኝተዋል:: ™ውሎስ ብዙ መጻሕፍትን ፅፈዋል፡፡

ጳውሎስ ከ1955 ዓ.ም ጀምሮ ለኢትዮጵያ ስነጽሑፍ ዕድገት የነበራቸውን ተሰጥኦ በአግባቡ በስራ ላይ ያዋሉ ዕውቅ ጋዜጠኛና ደራሲ ነበሩ::



**ደረጀ ውቤ ዳኘ** (1927 - )

ደረጀ ውቤ ዳኘ በሸዋ ጠቅላይ ግዛት በይፋት አውራጃ ጥር 24 ቀን 1927 ዓ.ም. ተወለዱ፡፡

ደረጀ ውቤ እድሜያቸው ለትምህርት በደረሰ ጊዜ አዲስ አበባ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን ተከታትለዋል:: ከዚያም ወደ ሐረር መምህራን ማሠልጠኛ በመሔድ ለሁለት ዓመታት ኮርስ ተከታትለዋል፡፡

ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በትምህርት ሚኒስቴር ተቀጥረው በተለያዩ ቦታዎች በመምህርነት አገልግለዋል፡፡ ከዚያም በማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ ገብተው በጋዜጣ ክፍል ውስጥ አገልግለዋል፡፡ በኢትዮጵያ ቱሪስት ድርጅትም ገብተው በቤተመጻሕፍት ውስጥ ሠርተዋል፡፡

ደረጀ ውቤ ዳኘ ከጻፏቸው መጻሕፍት ውስጥ በ1961 ዓ.ም. የፃፉት ∩የናርኮቲክ እመቤት∪ የተባለው ይገኝበታል፡፡



**ዳኛቸው ወርቁ (1928 - )**

***∩ በደራሲነት ስነፅሁፋዊ ቋንቋንና***

***አዲስ ዘዴን የሞከረና የፈጠረ ∪***

ዳኛቸው ወርቁ በ1928 ዓ.ም. ደብረሲና ተወለዱ፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በደብረሲና ካጠናቀቁ በኋላ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመግባት ትምህርታቸውን አጠናቀዋል፡፡ በ1953 ዓ.ም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ በመግባት የከፍተኛ ትምህርታቸውንም ጨርሰዋል፡፡ በዩኒቨርስቲ ቆይታቸውም በማኀበራዊ ጉዳዮች ላይ የተለያዮ የተቃውሞ ግጥሞችን ይጽ⌋ ነበር፡፡ ይህንንም በተመለከተ ስብስብ ሥራዎቻቸውንም ∩እምቧ በሉ∪ በሚል ርዕስ ስር መጽሐፍ አሳትመዋል፡፡

አቶ ዳኛቸው ወርቁ በአዲስ ዘመንና በየዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ላይ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ይጽፉ ነበር፣ የተለያዮ ቲያትሮችንም ይጽፉ ነበር፡፡ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንደምትቀላቀል በሚነገርበት ጊዜ ∩ያላቻ ጋብቻ ትር⌋ ሀዘን ብቻ∪ የሚል ቲያትር ሠርተው አቅርበው ነበር፡፡

ከአቶ ዳኛቸው ወርቁ ሥነ ጽሑፍ ሥራዎች መካከል በ1962 ዓ.ም. ለሕትመት የበቃው ∩***አደፍርስ***∪ የተሰኘው መጻሐፋቸው በጊዜው የነበረውን የመኳንንቱንና የባላባቱን የአኗኗር ሁኔታ እንዲሁም ስለ ሃይማኖት በሰፊው ይገልጻል፡፡ አደፍርስ /የታሪኩ ባለቤት/ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በመሆን ከአዲስ አበባ ወደ ባላገር በመሄድ በአንድ ላይ ቤት ተከራይተው መኖራቸውን በመተረክ በከተማውና በባላገሩ መካከል ያለውን ከፍተኛ የአስተሳሰብ፣ የልማድና የመሳሰሉትን ልዩነቶች በጉልህ ያስረዳል፡፡



**ደራሲ በዓሉ ግርማ (1928 - 1976 ዓ.ም)**

***∩ ትልቅ የስነ ፅሑፍ ሰው፣ ደራሲ ሆኖ የተፈጠረና ሰማዕት ∪***

ደራሲ በዓሉ ግርማ በኢሊባቡር ክፍለ ሀገር ሱጴ በምትባል ሥፍራ በ1928 ዓ.ም. ተወለዱ፡፡

ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በዘነበወርቅ ትምህርት ቤት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ በጀኔራል ዊንጌት አጠናቀዋል፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲም በፖለቲካል ሳይንስና ኢንተርናሽናል ሪሌሽን የቤ. ኤ. ዲግሪ ያገኙ ሲሆን ፣ በዚሁ ተመሣሣይ መስክ ከአውሮ± የማስተርስ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል ::

ደራሲ በዓሉ ግርማ በተለይ በልብወለድና በፈጠራ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ከታወቁት የኢትዮጵያ የዘመኑ ደራሲዎች መካከል ተወዳጅነትና ዝናን ያተረፉ እውቅ ደራሲ ነበሩ፡፡ ከጻፋቸው በርካታ ድርሰቶቻቸው ውስጥ ∩ ከአድማስ ባሻገር ∪የተሰኘው መጽሐፋቸው በሩሲያ ቋንቋ ተተርጉሞ በቀድሞዋ ሶ~የት ሕብረት ቀርቧል፡፡ በተጨማሪም በጋዜጠኝነት ሙያም ስማቸውን ያስጠሩ ሙያቸውንም ያስከበሩ ነበሩ፡፡ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ፣ የመነን መጽሔት ፣ የአዲስ ሪፖርት መጽሔት፣ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ በመሆን ከመሥራታቸውም ባሻገር ብዙ ወጣት ጋዜጠ→ችን ለማፍራት ጥረት አድርገዋል፡፡ አዲስ ሪፖርት የተባለውን መጽሔትም ደረጃው ከፍ እንዲልና በኢንተርናሽናል ደረጃ እንዲገመገም አድርገዋል፡፡ እንዲሁም በኢትዮጵያ ሬዲዮ ሠርተዋል፡፡ ደራሲ በዓሉ ግርማ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ከፍተኛውን አስተዋጽኦ ያበረከቱና ብዙ ሥራዎችን ያቀረቡ ሲሆን የመጨረሻው መጽሐፋቸው "ኦሮማይ" በመባል የሚታወቅ ሲሆን ፣ በወቅቱ በነበረው መንግስት ሊደገፍ ባለመቻሉ በ1976 ዓ.ም. ለደራሰው ሕይወት መጥፋት መንስኤ ሆኗል፡፡



**አማረ ማሞ አረሞ** (1939 - )

አቶ አማረ ማሞ በ1939 ዓ.ም. በሲዳሞ ተወለዱ፡፡ ዕድሜያቸው ለትምህርት በደረሰ ጊዜ ዳዊት መድገም ድረስ ተምረዋል፡፡ በመቀጠልም አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በማጠናቀቅ ከፍተኛ ትምህርታቸውን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተከታትለው በሥነ ጽሑፍ የቢ.ኤ. ዲግሪያቸውን አግኝተዋል፡፡

በሥራ ዓለም ላይም የሥነ ጽሑፍ ኃላፊ በመሆን በመሠራት በትርጉም ሥራ ተሳትፈዋል፡፡ደራሲ አማረ ማሞ የተለያዩ ድርሰቶችን በመድረስና የትርጉም መጻሕፍትንም በማዘጋጀት ብዙ መጻሕፍት አሳትመዋል ፡፡ አማረ ማሞ ከ1966 ዓ.ም በኋላም የተደረሱ ወጥ መጻሕፍቶችንም ከማሳተማቸውም በተጨማሪ ለሀገራችን የሥነ ጽሑፍ ዕድገትን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።



**ተስፋዬ አበበ ዳምጤ** (1931 - )

ተስፋዬ አበበ ዳምጤ በ1931 ዓ.ም. አዲስ አበባ ተወለዱ፡፡ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ገብረማርያም ትምህርት ቤት እስከ አሥራ አንደኛ ክፍል ተምረዋል፡፡

ተስፋዬ አበበ በ1947 ዓ.ም. በማዘጋጃ ቲያትር ቤት በተዋናይነት አገልግለው ብሔራዊ ቲያትር ሲቋቋም ከሥራተ→ቹ ጋር በመዛወር እስከ 1952 ዓ.ም. ድረስ አገልግለዋል። ከዚያም በክብር ዘበኛ ማስታወቂያ ክፍል በጋዜጠኝነት ለስድስት ወራቶች ሠርተዋል፡፡ በመቀጠልም በፖሊስ ሠራዊት ሙዚቃ ክፍል በደራሲነትና በአዘጋጅነት አገልግለዋል፡፡

ከጻፋቸው መጻሕፍት ውስጥ ፡-

- የአንድ ታላቅ ሰው ታሪካዊ የፈተና ጉዞ እና

በድል ጉዳና የተባሉት ይገኙበታል፡፡



**ግርማ ዳመኑ በጅቷል (1933 - )**

ደራሲ ግርማ ዳመኑ በጅቷል በ1933 ዓ.ም. ደብረዘይት ተወለዱ፡፡ዕድሜያቸውም ለትምህርት በደረሰም ጊዜ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በመከታተል አጠናቀቁ፡፡ በመቀጠልም ከፍተኛ ትምህርታቸውን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሕግ ትምህርት በመከታተል አጠናቀቁ፡፡

ደራሲ ግርማ ዳመኑ ከ1954ዓ.ም ጀምሮ የተለያዩ ድርሰቶችን በመድረስ መጻሕፍት አሳትመዋል፡፡ ከጻፉቸው መጻሕፍት ውስጥ ፡- ወንድምና እህት የንጋት ክዋክብት ፣ አንቺ የገዳም ተክል ፣ ወራሽ የሌለው ቤት፣ ድል በሰላም የተባሉ ይገኙበታል፡፡



**ፀጋዬ ገብረመድህን (ሎሬት) ( 1935-1998 ዓ.ም.)**

***∩ ገጣሚ፣ የትያትር ደራሲ፣ ዳይሬክተር ፣ተርጓሚ ባለቅኔና ተውኔት ፀሐፊ በቅድመ ጥንትና በጥንት በጥቁር የኢትዮጵያና የግብፅ ስነ ጥበብ የታሪክና የሰው ዘር አመጣጥ ተመራረማሪ ∪***

እውቁ ባለቅኔ ፀጋዬ ገ/መድኀን በ1935 አምቦ አካባቢ የተወለዱ ሲሆን ግማሽ ያህል ኪነ ጥበብ ሥራዎቻቸው በቲአትር ድርሰት ላይ ያተኮሩ ሲሆን በስነ ግጥምና በአፍሪካ የሥነ ጥበብ የምርምር ሥራዎቻቸውም ይታወቃሉ፡፡

ከ1950ዎቹ ጀምሮ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና የምሁራን እንቅስቃሴ ውስጥ እጅግ ታዋቂ እንደነበሩ ማንም እሚዘነጋው አይኖርም፡፡ ለዚህ ያበቃቸው ዋናው ምክንያት የኢትዮጵያን የቤተ ክህነት ትምህርት ጠለቅ ብለው ያጠኑ መሆናቸው ይህንንም በዘመናዊ ትምህርት አስደግፈው ስላሳደጉት ጭምር ነው፡፡

የመጀመሪያ ድርሰታቸውን በአሥራ አምስት አመታቸው ጽፈዋል፡፡ ሎሬት ፀጋዬ እ.ኤ.አ በ1959 ለትምህርት ወደ አውሮፖ ሄደው ከተመለሱ በኃላ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር ቤት ዳይሬክተር በመሆን የቲያትር ቤቱ ከፍተኛ ሥምና ዝና እንዲያገኝ አስችለዋል፡፡ በተከታታይ ልዩ ልዩ የቴአትር ስራዎቻቸውን

በማቅረብ በህዝብ ዘንድ ፀጋዬ የኢትዮጵያ ቴአትርን ለወጠው አስከመባል ደርሰዋል:: የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሽልማት ድርጅት ከስነጽሑፍ ተሸላሚዎች አንዱ ለመሆንም በቅተዋል::

ሎሬት ፀጋዬ በድርሰታቸው የሚነካኳቸው የህዝብ ቁስሎች መንግስትን እያስቆጡ በመሄዳቸው ለተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ እንዲጋለጡ ካደረጓቸውም በላይ ሥራቸውን እስከመልቀቅ መድረሳቸው ይታወሳል:: አንዳንድ የቲያትር ድርሰቶቻቸው ለህዝብ እይታ እንዳይቀርቡ የታገዱባቸው ባለቅኔ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድን በእሣት ወይ አበባ የግጥም መድብል የሚታወቁ ሰው ናቸው::

የእውቁ ደራሲ፣ ገጣሚና ባለቅኔ ፀጋዬ ገብረመድህን ስም ከኢትዮ}ያ ውጭ በአፍሪካ አልፎም በዓለም የታወቁና በአምስት ዓይነት ዓለም አቀፍ የ{ውቀት መመዝገቢያ መጻሕፍት የፀሐፊ ተውኔት፣ የባለቅኔዎች ፣ የመካከለኛ ምሥራቅ እውቅ ሰዎች፣ የአፍሪካ ዝነኛ ሰዎችና የዓለም አቀፍ & ሁ ኢዝ ሁ & ውስጥ ተመዝግቧል::

እኚህ አንጋፋ የጥበብ ሰው አርባ ያህል ቴአትሮች በአማርኛና በእንግሊዝኛ የደረሱና የተረጐሙ፣ በርካታ የአማርኛና የእንግሊዝኛ ቅኔዎች የፈጠሩ ፣ ሃያሦስት ወጥ ቴያትሮች ጽፈው ያቀረቡ ፣ ዘጠኝ የምርምር ጽሑፎችን ያቀረቡ፣ የኢንጂፐሮሎጂ / የጥንታዊ ጥቁር ግብጻውያን ጥናት/ ምሁር ናቸው:: ከሃያ ዘጠኝ የአማርኛ ቴአትሮቻቸው መካከል ሃያ ሦስቱ ወጥ ሲሆኑ የተቀሩት የሼክስፒር፣ ሞሊየርና የብሬክተን የመሳሰሉ ታላላቅ የሥነ ጥበብ ሥራዎችን ወደ አማርኛ የተረጐሙ ወይም ፍሬ ነገሮቹ ተወስደው የተጻ⌋ ናቸው:: ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን በሥነጽሑፍ ሥራዎቻቸው የአገር አቀፍና የዓለም አቀፍ ሽልማቶች ተሸላሚ ናቸው ::



**ሙላቱ ገብረ** (1937 - )

ደራሲ ሙላቱ ገብሩ 1937 ዓ.ም. ተወለዱ፡፡ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአሊያንስ ፍራንሴስ ትምህርት ቤት አጠናቀቁ፡፡ ከዚያም ወደ ፈረንሣይ አገር ሔደው ስለማዘጋጃ ቤቶች በምግብና በመጠጥ ምርመራ ትምህርት በዲፕሎማ ተመርቀዋል፡፡ ደራሲ ሙላቱ የድርሰት ዝንባሌ ስላላቸው የተለያዩ ድርሰቶችን በመድረስ መጻሕፍት አሳትመዋል:: በተጨማሪም የተለያዩ ቲያትር ድርሰቶችን ደርሰዋል፡፡ በሬዲዮ የተላለፉት ቲያትሮቻቸው መራራ ፍሬ ፣ ንፁህ ወንጀለኛ፣ የሞተ ሰው፣ ጥርሰ ወርቁ ፣ ሚስተር ↑ክሊን ፣ ከአብዮቱ ባሻገር ሲሆኑ በተጨማሪም በጋዜጣና በመጽሔት ላይ የተለያዩ ጽሑፎችን አቅርበዋል፡፡

ደራሲ ሙላቱ ገብረ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሑፍ ዕድገት ብዙ ሥራዎችን አበርክተዋል::

**ሲራክ ሂሩይ ወ/ስላሴ**

***∩ የአባቱን ፈለግ የተከተለ እና የአንድ መፅሐፍ ተርጓሚ ∪***

የአባታቸውን የሥነጽሑፍ ስራዎች በስራ ላይ ያዋሉ ፣ የአባታቸውን የሥነ ጽሑፍ ቅርሶች በጥንቃቄ ይዘው የቆዩ ፣ ከፊሎችን እንደገና ያሳተሙ ነበሩ፡፡ ከአለቃ ገብረሃና በኋላ እንደ ሲራክ ያሉ የሚያስቁ ቀልዶችን በሰፊው ያሠራጨና ያስተላለፈ ማንም ፀሐፊ የለም፡፡ ብዙዎቹ የሲራክ ሥራዎች ተረት ቢመስሉም ህብረተሰቡ ለሲራክ ያለው {ይታ ግን እንዲስማማ አድርጕቷል፡፡

ሲራክ መጀመሪያ ግ{ዝ ለመማር ወደ ደብረሊባኖስ ገዳም ተላኩ፡፡ ከዚያም አዲስ አበባ የሚሲዮኖች ት/ቤት ገቡ፡፡ ከዚያም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለመማር ወደ ግብ+ አሌክሳንድሪያ ኮሌፀ ሄዱ፡፡ ከኢጣሊያ ወረራ በኋላ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ እንግሊዝ ሀገር ሄዱ፡፡ አካሄዳቸውም በሱዳን በኩል ነበር፡፡ ሲራክ ፍልስፍናን ለመማር ኦክስፎርድ ዩኒቨርስቲ ገቡ፡፡

አፄ ኃይለሥላሴ በ1933 ዓ.ም. ከስደት ከተመለሱ በኋላ ሲራክ የሀገር ውስጥ ሚ/ር ፀሐፊ በመሆን ተሾሙ ፡፡ በዚህ በመንግሥት ሥራ ላይ እያገለገሉ ሳሉ ከብዙ ሚኒስትሮች ጋር ስለሚቀበሉት ጉቦና ሁኔታዎችን የማዘግየትና የማስተላለፍ ፖሊሲያቸውን አጥብቀው ይቃውሙ ነበር፡፡ ሲራክ እምቅ ዕወቀት እንዳላቸው ካላገናዘቡና ከንጉሱ ፖለቲከኞች ጋርም ለመጫወት ያልፈለጉ ሀቀኛ ሰው ነበሩ፡፡ ለንጉሡም ቢሆን ፖሊሲያቸውን እስካለወጡ በሀገሪቱ አብዮት እንደሚነሳባቸው ነግረዋቸው ነበር፡፡ በአርቆ አስተዋይነታቸው በሚፈፀሙት ጥፋቶች ሳለመጠየቅ ከመንግሥት ሥራ ለቀው ወጡ ፡፡

የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከኢትዮ}ያ ድንበር ውጭ በሚቀሰቀስባቸው አካባቢዎች ከአንድ እንግሊዝ ቆንስላ ውስጥ ከሚሰራና የእንግሊዝ የመረጃ አገልግሎት ሠራተኛ ከሆነ ሰው ተዋወቁ፡፡ ይህ ቢሮም ወደ &ድል ↓ዳና& የሚባል ወርሃዊ መጽሔት ያዘጋፀ ስለነበር ሲራክም አንዳንድ ጽሑፎችን በአማርኛ እየተረጐሙ ለማዘጋጀት ተቀጠሩ፡፡ በዚያን ጊዜ ነበር በእንግሊዝ ቆንስላ ውስጥ በመረጃ አገልግሎት ቢሮ ውስጥ የሚሠራው ምለሰ ዎርዝ የተባለው ሰው ሲራክን የዶክተር ሳሙኤል ጆንሰንን &ራሴላስ& እንዲተረጉሙ ያደረገው፡፡ ሲራክ ይህንን መጽሐፍ ሲተረጉሙ አማርኛውን በማረምና በማስተካከል ለሕትመት የሚያቀርቡትን ጹሁፎች ይረዷቸው የነበሩት በ{ደ ማሪያም ደስታ የሚባሉ ሰው ነበሩ፡፡ ሲራክ የሳሙኤል {ንሰንን በ1795 ዓ.ም. &ራሴላስ& እና &የአቢሲኒያው ልዑል& የተሰኘውን መጽሐፍ በመተር↓ም የሚታወቁ ሰው ነበሩ ፡፡ እኝህ ሰው በኢትዮ}ያ ስነ ጽሑፍ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጾ አድርገዋል፡፡